مركز عدالة لدراسات حقوق الإنسان
Adaleh center for human rights studies

PORTICUS

# ለቤት ሰራተኞች የወጡ መመሪያዎች (ዮርዳኖስ)



Designed by: A. A.GH

# ለቤት ሰራተኞች
# የወጡ መመሪያዎች
# (ዮርዳኖስ)

عدالة
مركز عدالة لدراسات حقوق الإنسان
Adaleh center for human rights studies

PORTICUS


EUROPE
Black Sea
Mediterranean
Sea
Jordan

# ለቤት ሰራተኞች የወጡ መመሪያዎች (ዮርዳኖስ)

ይህ ማኑዋል/መመሪያ የተለያዩ አገራት ዜግነት ላላቸው የቤት ሰራተኞች እና ለአሰሪዎቻቸው ስለ የቤት ሰራተኞች መብቶችና ግዴታዎች እና የባለድርሻ አካላት መብቶች ጥበቃን ለማሻሻል ሲባል የቤት ሰራተኞች እንዴት የተሻሻለ አያያዝ ማግኘት እንዳለባቸው የተመለከቱ መመሪያዎችን ይሰጣቸዋል።









1st
2nd
3rd

# መመሪያዎች

ይህ መመሪያ የቤት ሰራተኞች ከመጡ በኋላ ባለው ደንብ፣ ቅጥርና መመሪያ ላይ እንዲሁም ቅሬታዎች በቤት ሰራተኞችና አሰሪዎች ሪፖርት በሚደረጉባቸው ሥነ ሥርዓቶች ላይ ያተኩራል። መመሪያው ከዚህ ባሻገር ስለ ሕግ ምህዳሩ እና ስለ ዮርዳኖሳውያን ልማዶችና ባህሎች በተመለከተ የተግባር መረጃ የሚሰጥ ከመሆኑም በተጨማሪ የቤት ሰራተኞችን እና አሰሪዎችን ግንዛቤ የማሳደግ ዓላማ አለው።

## ይህ መመሪያ 3 ዋና ዋና ደረጃዎችን ያቀርባል

| | |
|---|---|
| 1 | መሰረታዊ የህግ መስፈርቶችን መረዳት እና የእነዚህን ተጽእኖ ለሰራተኞች ችግሮቻቸውን ለመፍታት በሚያግዛቸው አኳኋን ግልጽ ማድረግ። |
| 2 | የማህበራዊ ሥነ ህዝብ መስፈርቶችን መረዳት እና የሥደተኛ ሰራተኞችን እውቀትና ችሎታዎች ማሳደግ። |
| 3 | የኢኮኖሚ እና የፋይናንስ መስፈርቶችን መረዳት እና ለቤት ሰራተኞች መብቶች የሚደረገውን ጥበቃ በተሻለ ሁኔታ ማሳደግ። |


EUROPE
Black Sea
Mediterranean
Sea
Jordan

# የማህበራዊ ሥነ ህዝብ ገጽታዎች

## የዮርዳኖስ ሥነ ሕዝብ

- ዮርዳኖስ፥ በእሲያ/ምዕራብ እሲያ አህጉር ውስጥ ትገኛለች
- የዮርዳኖስ ዋና ከተማ፥ አማን
- የዮርዳኖስ ሕጋዊ የመገበያያ ገንዘብ፥ የዮርዳኖስ ዲናር
- የዮርዳኖስ የህዝብ ብዛት ወደ 11 ሚሊዮን ያክል እንደሚሆን ይገመታል

## ሀይማኖት እና ቋንቋ

በዮርዳኖስ ውስጥ ያሉ ቋንቋዎችና ሀይማኖቶችን በተመለከተ የአገሪቱ ኦፊሴላዊ ቋንቋ አረቢኛ ሲሆን በመጀመሪያ የሚነገረው የውጭ አገር ቋንቋ እንግሊዘኛ ነው። ሙስሊሞች ከህዝብ ቁጥሯ ውስጥ አብላጫውን ድርሻ የሚይዙ በመሆኑ ምክንያት እስልምና የዮርዳኖስ ኦፊሴላዊ ሀይማኖት ሲሆን ቀጥሎም ክርስትና ይመለካል። ሀይማኖታዊ ተግባራት የሚተገበሩባቸው መስኪዶች እና አብያተ ክርስትያናት ያሉ ቢሆንም አብያተ ክርስትያናት በዋና ዋና ከተሞች ተሰባጥረው ይገኛሉ።

## የዮርዳኖሳውያን አመጋገብ

ዳቦ የተወሰኑ ምግቦችን ብቻ ከዳቦ ጋር አብረው ለሚመገቡ ዮርዳኖሳውያን ዋነኛው የምግብ ግብዓት ነው። በዮርዳኖሳውያን ዘንድ በጣም ተወዳጅ እና የአብዛኞቹ ምግቦች ዋነኛ ግብአት ከሆኑት ምግቦች መካከል አንደኛው ሩዝ (ማንሳፍ፣ ማቅሉባ፣ አውዚ) ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ጥራጥሬዎች፣ የወይራ ፍሬዎች፣ የወይራ ዘይት፣ እርጎ፣ አትክልት (አበባ ጎመን፣ መደረቻ፣ ድንቾች፣ አክራ፣ ቲማቲሞች እና የፈረንጅ ዱባ)፣ የበግ ስጋ ወይም የዶሮ ስጋ እና ፍራፍሬ ናቸው። ማንሳፍ የዮርዳኖስ ዋነኛው ምግብ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን በአብዛኛው አርብ አርብ እለት ይበላል። ማንሳፍ በዮርዳኖስ ውስጥ በጣም ከተለመዱት እና ተወዳጅ ከሆኑት ምግቦች መካከል አንዱ ሲሆን በደስታና ሀዘን ወ ቅት (በሀዘን ቤት፣ የበዓል ቀናት፣ ለሰርግ) እንደሚቀርብ መሰረታዊ ምግብ ተደርጎ ይቆጠራል። አብዛኞቹ ዮርዳኖሳውያን የአሳማ ስጋም ሆነ የአልኮል መጠጥ አይወስዱም።





## ልማዶች እና ባህሎች

በተጨማሪም በአረብ ክልል ውስጥ ያሉ እንደ ለጋስነት፣ እንግዳ ተቀባይነት እና ለሌሎች ቀና አቀባበል ማድረግ የመሳሰሉ የአረብ ልማዶች ዮርዳኖስ ውስጥም አሉ። ዮርዳኖስን ልዩ የሚያደርጋት ባህሎቿ አንድ አይነትና ድብልቅ መሆናቸው ነው። በአጠቃላይ ቡና እጅግ ለረጅም ጊዜ ከሚዘወተሩ የዮርዳኖሳውያን እሴቶችና ባህሎች መካከል አንዱ ነው።

## የዮርዳኖስ አየር ንብረት

ዮርዳኖስ ከምትገኝበት ልዩ ጂኦግራፊያዊ አቅጣጫ አንጻር የተመጣጠነ የአየር ንብረት ያላት ሆኖ በዓመት ውስጥ አራት ወቅቶች አሏት። በጋ ሞቃት ወቅት እና ክረምት በከፍታማ ቦታዎች ቀዝቃዛው ወቅት ሲሆን በዮርዳኖስ ሸለቆና ዙሪያ የሚገኙና ዝቅተኛ ቦታዎች ሞቃት የበጋ ወቅትና በመጠኑ ሞቃት የክረምት ወቅት አላቸው።







## የዮርዳኖስ በዓላት

በእጅጉ የሚታወቁት ሀይማኖታዊ ወቅቶችና ሀይማኖታዊ በኣላት የሙስሎሞችን ኢድ አል ፈጥርና ኢድ አል አድሀን እንዲሁም የክርስትያኖችን የገና በዓልና የፋሲካ በዓልን ያጠቃልላሉ። በዋናነት ዮርዳኖስ ውስጥ ሰዎች በዓላትን ዘመዶቻቸውን እና ጎረቤቶቻቸውን ሄደው ለመጠየቅ ይጠቀሙባቸዋል። አብዛኞቹ ቤተሰቦች የኢድ ቀናት አፊሴላዊ የበዓል ቀናት በመሆናቸው ምክንያት የሚጠያየቁት በኢድ ወቅት ሲሆን እነዚህን ቀናት በመደበኛ ቀናት ለመጠየቅ የሚከብዳቸው ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ይጠቀሙባቸዋል።

## አገልግሎትና ሀይማኖታዊ ተግባሮች

ለቤት ሰራተኞች የማህበረሰቡን ህጎችና ሞራል ባከበረ መልኩ ሀይማኖታዊ ተግባሮቻቸውን መከወን የሚያስችላቸው በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀና በአግባቡ አየር የሚያስገባ ክፍል መዘጋጀት አለበት። ዮርዳኖስ ውስጥ ሀይማኖታዊ ተግባሮች የሚካሄዱባቸው ቤተ መቅደሶች የሉም።

## በዮርዳኖስ ቤተሰብ

ዮርዳኖስ ውስጥ አብዛኞቹ ቤተሰቦች ባል፣ ሚስትና ልጆች ያሉባቸው ናቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች የልጅ ልጆችን እና ያገቡ ልጆችን የሚያካትቱ ቤተ ዘመዶች በቤተሰብ ውስጥ ወይም በአጎራባች በሚገኙ ቤቶች ውስጥ ይኖራሉ።



عدالة
مركز عدالة لدراسات حقوق الإنسان
Adaleh center for human rights studies

جمعية اتحاد المرأة الأردنية

تمكين
TAMKEEN
fields for aid | للدعم والمساندة

اللجنة الوطنية لمنع الاتجار بالبشر
Anti-human Trafficking National Committee

وزارة العمل

# ለቤት ሰራተኞች የህግ እገዛ የሚያቀርቡ ተቋማት

| አዳል የሰብዓዊ መብቶች ጥናቶች ማዕከል |
| --- |
| አዳል ማዕከል (Adaleh Center) ለስደተኛ ሰራተኞችና የቤት ሰራተኞች የህግ እገዛ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ይሰራል። ክፍሉ የሚከተሉትን ለማድረግ ይሰራል |
| • ለስደተኛ ሰራተኞችና የቤት ሰራተኞች ስለ መብቶቻቸው እና ፍዴታዎቻቸው እንዲሁም አሰሪዎቻቸው በእነሱ ላይ ስላሏቸው መብቶችና ስላሉባቸው ግዴታዎች ለማስተዋወቅ። |
| • የስደተኛና የቤት ሰራተኞች መብቶችን ለመከላከል እና ለሰራተኞቹ በተለያዩ መንገዶች የህግ እገዛ ለማቅረብ። |
| • የጸጥታ APBዎችን (የአውሮፕላን ማረፊያ APBዎች) ለማስቀረት ከጸጥታ ማእከላት ጋር ክትትል ለማድረግ። |
| • አለመግባባቶችን በቀና መንፈስ እና ለሁለቱም ወገኖች አመርቂ በሆነ አኳኋን ለመፍታት አሰሪዎችን ለማነጋገር። |
| • በስራ ፍቃዶች መሰጠት ወይም መታደስ ላይ ከሰራተኛና አሰሪ ሚኒስቴር ጋር ክትትል ለማድረግ። |
| • በነዋሪነት ፍቃዶች መታደስ ላይ ከድንበርና የነዋሪነት መምሪያ ጋር ክትትል ለማድረግ። |
| • የይቅርታ ህጎች ተፈጻሚ በሚሆኑበት ወቅት ውስጥ እነዚህን ለማጠናከር ትኩረት ለሚደረግበት ቡድን በሚጠቅም መልኩ ማንኛውንም አስተዳደራዊ፣ የዳኝነት ወይም ሌሎች እርምጃዎችን ለመውሰድ። |

## የክፍሉ የአሰራር ዘዴዎች

- የሥደተኛ ሰራተኞችና የቤት ሰራተኞች የመብቶች ጥሰትን የሚይዙ ጉዳዮችን በተመለከተ በተለይም የፓስፖርታቸው መያዝ/ጥቃት ወይም አካላዊ ጥቃትን የሚይዙ ጉዳዮችን በተመለከተ ከስደተኛና የቤት ሰራተኞቻቸው እና ጠበቆቻቸው ቅሬታዎችን መቀበል።
- የሥራ ቦታዎችን፣ ኢምባሲዎችን፣ የፀጥታ ማእከላትን፣ የማሻሻያና ማረሚያ ማእከላትን ጨምሮ ስደተኛ ሰራተኞችና የቤት ሰራተኞች ሊገኙ የሚችሉባቸውን ቦታዎች መጎብኘት እና የህግ እገዛ፣ የምክርና ማማከር አገልግሎት መስጠት።
- ሰራተኞች የይቅርታ ሕጉን መጠየቅ በሚችሉባቸው ወቅቶች ውስጥ ለስደተኛ ሰራተኞችና የቤት ሰራተኞች የህግ እገዛና ምክር ለማቅረብ ከባለድርሻ አካላት (የሰራተኛና አሰሪ ሚኒስቴር፣ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር) ጋር ክትትልና ትብብር ማድረግ።
- ሰራተኞችን ለሚልኩ አገራት ስለ ስደተኛ ሰራተኛና የቤት ሰራተኛ የህግ እገዛ ክፍሉ ስራና ዓላማዎች ለማሳወቅ፣ የትብብር አሰራር ዘዴ ለማዘጋጀት እና መብቶቻቸውን በአዎንታዊ መልኩ ተፈጻሚ ለማድረግ በቅንጅት ለመስራት ለሰራተኞችን የሚልኩ አገራት ኢምባሲዎችን ማነጋገር።
- በአንዳንድ ሁኔታዎች የስደተኛና የቤት ሰራተኞች ጉዳዮችን በተመለከተ ስልጣን በተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች ፊት መሟገት።

የህግ እገዛ ማግኘት ካስፈለግዎ እባክዎ የአዳል የሰብዓዊ መብቶች ጥናቶች ማዕከልን (Adaleh Center for Human Rights Studies) የህግ ክፍል መ/ቤት ይጎብኙ።

# አዳል የሰብዓዊ መብቶች ጥናቶች ማዕከል

## መገኛ ቦታ

አማን - ቲላ አል አሊ - ከግብርና ሚኒስቴር በስተጀርባ - አል ማዋርዲ መንገድ - ህንጻ ቁ. (4)።

## የግንኙነት መረጃ

| | |
|---|---|
| የማዕከሉ ስልክ ቁጥር፥ | 065602371 |
| የክፍሉ ስልክ ቁጥር፥ | 0796159666 |




عدالة
مركز عدالة لدراسات حقوق الإنسان
Adaleh center for human rights studies



# የዮርዳኖሳውያን ሴቶች ህብረት ስራ ማህበር


## መገኛ ቦታ

ጀበል አል-ሁሴኒ ሳፋድ መንገድ - ከሱካይና ትምህርት ቤት በስተጀርባ።

## የግንኙነት መረጃ

| | |
|---|---|
| ስልክ-የአስተዳደር፥ | 065687037 |
| ስልክ - የመመሪያ መስመር፥ | 065675729 |
| የእንግዳ ማረፊያ ስልክ፥ | 065689522 |



# ታምኪን የህግ እርዳታና ሰብዓዊ መብቶች


## መገኛ ቦታ

አማን፣ አል-መዲና አል-ሙናዋራ መንገድ፣ ህንጻ 197፣ ሶስተኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁ. 306-307

## የግንኙነት መረጃ

| | |
|---|---|
| የማዕከሉ ስልክ ቁጥር፦ | 065539501 |
| የሞባይል ቁጥር፦ | 0796404406 _ 0788510027 _ 0775222070 |





# የሰዎች ዝውውር ክፍል

| | |
|---|---|
| **መገኛ ቦታ** | |
| አማን _ ካልዳ | |
| **የግንኙነት መረጃ** | |
| **የቀጥታ መስመር ቁጥር፥** | 911 |
| **የእርዳታ መስመር ቁጥር፥** | 065530266 |




اللجنة الوطنية لمنع الاتجار بالبشر
Anti-human Trafficking National Committee



# የሠራተኛ ሚኒስቴር

## መገኛ ቦታ

7ኛ ሰርክል _ ኢሳ አል-ኑሪ መንገድ

## የግንኙነት መረጃ

| | |
|---|---|
| ስልክ ቁጥር፥ | 062221020 |
| ብሔራዊ የጥሪ ማዕከል፥ | 0650088080 |









# ኢምባሲዎችና ለዜጎቻቸው የሚያቀርቧቸው አገልግሎቶች

| በኢምባሲዎች ለዜጎቻቸው የሚቀርቡ አገልግሎቶች |
|---|
| • ኢምባሲ የዜጎችን መብቶች ለማስከበር ይሰራል |
| • ኢምባሲ ዜጎቹን የሚያጋጥሟቸውን ማንኛውንም ችግሮች ወይም ጥሰቶች ለመፍታት ለዜጎቹ እገዛ ያደርጋል። |
| • ኢምባሲ ዜጎቹን ወደ አገራቸው ለመመለስ፣ ፓስፖርቶቻቸውን ለማደስ እና አስፈላጊ ሰነዶች እንዲሰጧቸው ለዜጎቹ እገዛ ያደርጋል። |





# ኢምባሲዎችና የግንኙነት መረጃ፥

| 1 | የባንግላዲሽ ህዝባዊ ሪፑብሊክ ኢምባሲ |
|---|---|
| መገኛ ቦታ | |
| ኡም ኦታንያ-ኢብራሂም አል-ጋዛላኒ- ቪላ ቁ. 7 | |
| የግንኙነት መረጃ | |
| ስልክ ቁጥር፥ | 065529192 |
| ኢሜይል፥ | embangl@wanadoo.jo |







## 2 Embassy of the Democratic Socialist Republic of Sri Lanka

| መገኛ ቦታ | |
|---|---|
| አማን _ አል መዲና አል-ሙናዋራ መንገድ _ ከአል-ራዋሽህ ማዕከል ህንጻ ቀጥሎ | |
| **የግንኙነት መረጃ** | |
| **ስልክ ቁጥር፥** | 582061506 |
| **ኢሜይል፥** | lankaembjo@orange.jo |





| 3 | የፊሊፒንስ ሪፑብሊክ ኢምባሲ |
|---|---|
| መገኛ ቦታ | |
| አማን _ አብዱን _ ሳታን አል-ሀሰን መንገድ _ ቪላ ቁ. 16 | |
| የግንኙነት መረጃ | |
| ስልክ ቁጥር፥ | 065901730 |
| ኢሜይል፥ | ammanpe@orange.jo |









| 4 | የኢትዮጵያ ቆንስላ |
| --- | --- |
| መገኛ ቦታ | |
| አማን_ረቢ_አህመድ አል-ነጃዊ መንገድ ህንጻ ቁ. (37) | |
| የግንኙነት መረጃ | |
| ስልክ ቁጥር፥ | 0779909990 |
| ኢሜይል፥ | info@ethioconsulatejo.com |








## 5 የኔፓል ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ኢምባሲ

### መገኛ ቦታ

አማን ውስጥ ኢምባሲ የለውም፣ ሆኖም ሪያድ-ሳውዲ አረቢያ ኪንግደም (KSA) የሚገኘውን ኢምባሲ ማነጋገር ይቻላል።

### የግንኙነት መረጃ

| | |
|---|---|
| ስልክ ቁጥር፦ | 14611108 (00966 ) |
| ኢሜይል፦ | info@rneksa.org |









## 6 የዑጋንዳ ሪፑብሊክ ኢምባሲ

### መገኛ ቦታ

አማን ውስጥ ኢምባሲ የለውም፣ ሆኖም ሪያድ-ሳውዲ አረቢያ ኪንግደም (KSA)
የሚገኘውን ኢምባሲ ማነጋገር ይቻላል።

### የግንኙነት መረጃ

| | |
|---|---|
| ስልክ ቁጥር፥ | 4544910 (009661 ) |
| ኢሜይል፥ | ugariyadh@hotmail.com |










THE HASHEMITE KING
CENTRAL BANK O
JORDAN
البنك المركزي الأردني
عشرون دينارا
خمسون دينارا

## ኢኮኖሚያዊ ገጽታዎች


| በዮርዳኖስና በላኪ አገራት መካከል በሚደረጉ የሁለቲዮሽ ስምምነቶች ላይ ተመስርተው ለቤት ሰራተኞች የሚከፈሉ የደመወዝ ክፍያዎች | | |
|---|---|---|
| # | ዜግነት | ደመወዝ |
| 1 | ጋና | $250 (ልምድ ላለው) |
| | | $225 (ልምድ ለሌለው) |
| 2 | ባንግላዲሽ | $250 (ልምድ ላለው) |
| | | $225 (ልምድ ለሌለው) |
| 3 | ፊሊፒንስ | $400 |
| 4 | ኢትዮጵያ | $250 (ልምድ ላለው) |
| | | $225 (ልምድ ለሌለው) |
| 5 | ኔፓል | $300 |
| 6 | ዑጋንዳ | $250 (ልምድ ላለው) |
| | | $225 (ልምድ ለሌለው) |

የቤት ሰራተኞች የዮርዳኖሳውያን ዝቅተኛ ደመወዝ JD260 ወይም ተመጣጣኙ $366 ስለማይመለከታቸው ከእነዚህ ነጻ ናቸው።

## የቤት ሰራተኞች የሥራ ፍቃድ ክፍያዎች ወጪ (ዲናር) በዓመት

| # | ልምዶች | ዜግነት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ኢትዮጵያ | ጋና | ዑጋንዳ | ባንግላዲሽ | ፊሊፒንስ | ኔፓል |
| 1 | የሥራ ፍቃድ ክፍያዎች | 430 | 430 | 430 | 430 | 430 | 430 |
| 2 | የህክምና ምርመራ ክፍያዎች/የጤና ሚኒስቴር | 85 | 85 | 85 | 85 | 85 | 85 |
| 3 | የመኖሪያ ፍቃድ ክፍያዎች/የድንበርና ነዋሪነት መምሪያ | 31 | 31 | 31 | 31 | 31 | 31 |
| 4 | የንግስት አሊያ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ የመግቢያ ቪዛ ክፍያዎች | 40 | 40 | 40 | 40 | 40 | 40 |
| 5 | የመድን ዋስትና ፖሊሲ | 25 | 25 | 25 | 25 | 25 | 25 |








## የአሰሪ ክፍያ

መ/ቤቱ በሁለተኛው ዓመት ሰራተኛውን አንዴ የሥራ ፍቃዱ ካበቃ በኋላ ወደ ሌላ አሰሪ ቤት ለማዛወር ለሚፈል አሰሪ ሰራተኛው በአዲሱ አሰሪው ቤት መስራት ከሚጀምርበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ወር በኋላ ለአሰሪው ከታች የተገለጸውን የገንዘብ መጠን በሚከተለው መልኩ የመክፈል ግዴታ አለበት፥

| ዜግነት | ኢትዮጵያ | ጋና | ዑጋንዳ | ባንግላዲሽ | ፊሊፒንስ | ኔፓል |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በዮርዳኖስ ዲናር | 500 | 500 | 500 | 600 | 1200 | 1000 |







# የህግ ገጽታዎች

## 1. ሰራተኛው መብቶቹን ለመጠየቅ ምን መረጃና ሰነዶችን ማስቀመጥ አለበት?

- የሥራ ቅጥር ውል
- የአሰሪ ሙሉ ስም
- የሰራተኛው የግል ቁጥር
- የሰራተኛው ፓስፖርት /የጉዞ ሰነድ/
- የሥራ ፍቃድ
- የሥራ ቦታ

## 2. ሰራተኛው የቅጥር ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት?

ሠራተኛው ለቀጣሪ መሥሪያ ቤቱ ወይም ለአሰሪዎች ምንም ገንዘብ መክፈል የለበትም።

**3. ቀጣሪ መስሪያ ቤቱ ስራቸውን ለሚለቁ እና ከአሰሪያቸው ጋር የገቡትን የስራ ውል የቆይታ ጊዜ ለማጠናቀቅ ፍቃደኛ ለማይሆኑ ሰራተኞች የጉዞ ቲኬት የማዘጋጀት ግዴታ አለበት?**

አዎ፤ ሰራተኛው ለመስራት ፍቃደኛ የማይሆን እና አገሪቱን ለቆ መውጣት የሚፈልግ ከሆነ እቢታውን ያሳወቀው ሰራተኛው ወደ አገሪቱ በገባ በ90 ቀናት ውስጥ ወይም ወደ አሰሪው ቤት በገባ በ30 ቀናት ውስጥ መሆን ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀጣሪው መ/ቤት በራሱ ወጪ የሰራተኛውን የጉዞ ቲኬት የመሸፈን ግዴታ አለበት።

**4. የቤት ሰራተኞች በAPB ጊዜ ከሚሰሩበት ቤት ከመቅረታቸው ወይም በሌላ ዘርፍ ላይ ከመስራታቸው ጋር በተገናኘ ሊታሰሩና ከአገር ሊባረሩ ይችላሉ?**

አዎ፤ ሰራተኛው በAPB በማይገኝበት ሁኔታ በሌላ ዘርፍ ላይ ሲሰራ ቢገኝ የሰተራተኛውን ከአገር መባረር ወይም ስጋትነት በተመለከተ በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም በሰራተኛና አሰሪ ሚኒስቴር ውሳኔ ይተላለፋል።

**5. ዮርዳኖሳውያን ያልሆኑ የቤት ሰራተኞች ወደ ሌሎች ዘርፎች መዛወር ይፈቀድላቸዋል?**

የቤት ሰራተኞች ወደ ሌሎች የስራ ዘርፎች አይዛወሩም።

6. የቤት ሰራተኞች በአሰሪያቸው ወጪ ውጭ አገር ለሚገኙት ቤተሰቦቻቸው መደወል ይፈቀድላቸዋል?

አዎ፤ ሰራተኛው በወር አንድ ጊዜ ውጭ አገር ለሚገኝ ቤተሰቡ በአሰሪው ወጪ እና ሰራተኛው ከፈለገ በራሱ ወጪ ብዙ ጊዜ ስልክ የመደወል መብቱ የተጠበቀ ነው።

7. አሰሪው ለሰራተኛው የበረራ ቲኬት ወጪውን የመክፈል ግዴታ አለበት?

አዎ፤ ሰራተኛው ሁለት ዓመት ከሰራ በኋላ።

8. ሰራተኛው የእረፍት ቀን የማግኘት መብት አለው?

አዎ፤ ይህ ቀን በሰራተኛውና አሰሪው መካከል በሚደረግ ስምምነት ይወሰናል።

9. ሰራተኛው የዓመት እረፍት የማግኘት መብት አለው?

አዎ፤ ሰራተኛው ከአሰሪው ጋር በሚደረግ ስምምነት በዓመት የ14 ቀናት እረፍት ከክፍያ ጋር የማግኘት መብት አለው። የሰራተኛውን የዓመት እረፍት ቀናት ወደ ሰራተኛው ውል ማብቂያ የማስተላለፍ ስምምነት ሊደረግ ይችላል።

## 10. ዮርዳኖስ ውስጥ የስፖንሰርሺፕ ስርዓቱ ከአንድ አሰሪ ወደ ሌላ አሰሪ መዛወርን ይፈቅዳል?

ስደተኛ ሰራተኛው ያለ የመጀመሪያ አሰሪው ፍቃድ ከአንድ አሰሪ ወደ ሌላ አሰሪ መዛወር አይችልም።

## 11. የቤት ሰራተኞች ምን ያክል ሰዓቶች የመስራት ግዴታ አለባቸው?

የሰራተኛውን የማረፊያ ወይም የመመገቢያ ሰዓቶች ሳይጨምር ሰራተኛው በቀን ውስጥ የቤት ውስጥ ስራዎችን በትክክል የሚሰራባቸው ጠቅላላ ሰዓቶች 8 ሰዓቶች ናቸው።







## 12. ሰራተኛው ከክፍያ ጋር የህመም እረፍት የማግኘት መብት አለው?

አዎ፤ ሰራተኛው በዓመት የ14 ቀናት የህመም እረፍት ከክፍያ ጋር የማግኘት መብት አለው።

## 13. የቤት ሰራተኛ መብቶች ምንድን ናቸው?

አንድ የቤት ሰራተኛ በክብር የመስተናገድ እና ተስማሚ የስራ መስፈርቶችና ድንጋጌዎች የማግኘት እንዲሁም አልባሳትን፣ ምግብን፣ መጠጥን፣ በአግባቡ የተዘጋጀና አየር የሚያስገባ ክፍልን፣ መኝታና የመኝታ ልብሶችን፣ የግላዊነት መብትን እና የህብረተሰቡን ህግና ሞራሎች ባከበረ መልኩ ሀይማኖታዊ ተግባሮችን የሚከውንበት ፍቃድ ማግኘትን ጨምሮ ሁሉም መሰረታዊ ፍላጎቶቹ እንዲሟሉለት የማድረግ መብት አለው።

## 14. የቤት ሰራተኞች የደመወዝ ክፍያዎች የሚከፈሉት መቼና እንዴት ነው?

የአንድ ሰራተኛ ወርሀዊ የደመወዝ ክፍያ የሚከፈለው ለዚህ ዓላማ በሚኒስቴሩ የሚወሰኑትን የክፍያ ዘዴዎች በመጠቀም የሰራተኛው ወርሀዊ ደመወዝ ገቢ የሚደረግበት የባንክ ሂሳብ በመክፈት ወይም በሰራተኛው ጥያቄ ወርሀዊ ደመወዙን ወደ ትውልድ አገሩ በመላክ መሆኑ እና አሰሪው የሰራተኛውን ወርሀዊ ደመወዝ መክፈሉን የሚያረጋግጡ የማንኛውንም ሰነዶች ኮፒዎች መያዝ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መከፈል ካለበት ቀን ጀምሮ በሰባት ቀናት ውስጥ በዮርዳኖስ ዲናር ወይም በተመጣጣኙ የውጭ አገር ገንዘብ መከፈል አለበት።

## 15. አንድ ሰራተኛ የደመወዝ ተቀናሾች የሚቀነሱበት መቼ ነው?

ሰራተኛው የአሰሪው ንብረት የሆኑ ወይም በአሰሪው ይዞታ ስር ባሉ፣ ወይም ለሰራተኛው ለስራ በተሰጡት እቃዎች፣ ማሽኖች ወይም ምርቶች ላይ በሰራተኛው ስህተት ወይም የአሰሪውን መመሪያዎች በመጣሱ ምክንያት ኪሳራ ወይም ውድመት እንዲደርስ ማድረጉ ከተረጋገጠ የሚደረገው ተቀናሽ ከሰራተኛው የ5 ቀን ወርሀዊ ደመወዝ መብለጥ የሌለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አሰሪው ከሰራተኛው ደመወዝ ላይ የጠፋውን ወይም የተጎዳውን እቃ ዋጋ ወይም የእቃውን የጥገና ወጪ ሊቀንስ ይችላል። አሰሪው በተጨማሪም በሰራተኛው ለደረሰው ጉዳት የካሳ ክፍያ ለማስከፈል ጉዳዩን ስልጣን ወደተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች ሊወስድ ይችላል።

## 16. አሰሪው የሰራተኛውን የስራ ፍቃድና የመኖሪያ ፍቃድ ክፍያዎች የመክፈል ግዴታ አለበት?

አሰሪው የሰራተኛውን የመኖሪያና የሥራ ፍቃድ ማውጫ እንዲሁም ዓመታዊ የማደሻ ክፍያዎች የመክፈል ግዴታ አለበት።

## 17. አሰሪው ሰራተኛውን ሌላ ቤት የማሰራት መብት አለው?

አሰሪው ሰራተኛውን ከቤተሰቡ ጋር ከሚኖርበት መደበኛ ወይም ጊዜያዊ መኖሪያ ውጭ በማንኛውም ሌላ ቦታ ማሰራት አይችልም።

### 18. አሰሪው ሰራተኛውን ወደ ሌላ አገር ለስራ ይዞ የመሄድ መብት አለው?


አሰሪው ሰራተኛውን ለጊዜያዊ ቆይታ ብቻ በሰራተኛው ፍቃድ እና ለሰራተኛው አገር ኢምባሲ ካሳወቀ በኋላ ወደ ሌላ አገር ይዞት ሊሄድ ይችላል።

### 19. ስራቸውን የሚለቁ ሰራተኞች የቅጥርና የጉዞ ቲኬት ወጪያቸውን የመሸፈን ኃላፊነት አለባቸው?

አዎ፤ ሰራተኛው ያለ ምክንያት ወይም አሳማኝ ማስረጃ ስራውን የሚተው/የሚለቅ ከሆነ በፈረመው የሥራ ውል መሰረት ሁሉንም የገንዘብ ግዴታዎቹን እና ወደ አገሩ መመለሻ ወጪውን የመክፈል ኃላፊነት አለበት።





| 20. የቤት ሰራተኞች ግዴታዎች ምንድን ናቸው? | |
|---|---|
| 1 | የቤት ውስጥ ስራ በታማኝነትና በትጋት መስራት። |
| 2 | የሚሰሩበትን ቤት ግላዊነት ማክበር እና የሚሰሩበትን ቤት ባለቤት ንብረቶችና የቤቱን ይዘቶች መጠበቅ። |
| 3 | ያወቋቸውን ሚስጥሮች አለመግለጽ። |
| 4 | የማህበረሰቡን ነባር ልማዶችና ባህሎች ማክበር። |
| 5 | ከሚሰሩበት ቤት ከመውጣታቸው ወይም ከመቅረታቸው በፊት ለቤቱ ባለቤት ማሳወቅ። |

| 21. አሰሪዎች የሰራተኞችን የጉዞ ሰነድ /ፓስፖርት/ እና ህጋዊ ሰነዶች የመያዝ መብት አላቸውን? |
|---|
| አሰሪዎች የሰራተኞችን ፓስፖርትና ህጋዊ ሰነዶች የመያዝ መብት የላቸውም። |

| 22. አሰሪው ለሰራተኛው የጤና እንክብካቤ የማቅረብ ግዴታ አለበትን? |
|---|
| አዎ፤ አሰሪ ለሰራተኛው የጤና እንክብካቤ የማቅረብ ግዴታ አለበት። |

## 23. ሰራተኛው በአሰሪው መብቶቹ በመጣሳቸው ምክንያት ስራውን የሚለቅ ከሆነ ሰራተኛው ሊከተላቸው የሚገቡ ሥነ ሥርዓቶች ምንድን ናቸው?

በተቻለ መጠን የመብት ጥሰቱን በሰራተኛው ኢምባሲ፣ የሰራተኛና አሰሪ ሚኒስቴር እና በዚህ መስክ በንቃት እየሰሩ በሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት በኩል ሪፖርት ማድረግ።

## 24. የቤት ሰራተኞች በማህበራዊ ዋስትና ድንጋጌዎች ውስጥ ይሸፈናሉን?

እስከ አሁን ድረስ የቤት ሰራተኞች በማህበራዊ ዋስትና ድንጋጌዎች ውስጥ አይሸፈኑም።





## 25. ሕጉ የሥራ ላይ ጥቃትን እና ትንኮሳን ወንጀል ያደርጋል?

**አዎ፤ ማንኛውም በቤት ሰራተኞች ላይ በቤት ባለቤቶች ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው የሚፈጸሙ የጥቃት ወይም የትንኮሳ ድርጊቶች በወንጀል ያስቀጣሉ።**

## 26. ሰራተኛው አካላዊ፣ ወሲባዊ ወይም የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚደርስበት ከሆነ ስራውን የመተው/የመልቀቅ መብት አለው?

**አዎ፤ ሰራተኛው ማንኛውም አካላዊ ወይም የወሲብ ጥቃት የሚደርስበት ከሆነ ስራውን የመተው እና ካሳ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው።**

## 27. ለሰራተኛው በትውልድ አገሩ ወይም ተቀባዩ አገር ለሚሰጥ ስልጠና በምላሹ ከሰራተኛው ደመወዝ ላይ መቀነስ ይፈቀዳል?

**ለሰራተኛው በትውልድ አገሩ ወይም በሚሰራበት አገር ለሚሰጥ ስልጠና በምላሹ ከደመወዙ ላይ ምንም የገንዘብ መጠን መቀነስ የለበትም።**



| ለበለጠ መረጃ<br>እባክዎን የአዳላህ የሰብአዊ መብቶች ጥናት ማእከልን ያነጋግሩ | |
|---|---|
| መገኛ ቦታ | አማን - ቲላ አል አሊ - ከግብርና ሚኒስቴር በስተጀርባ - አል ማዋርዲ መንገድ - ህንጻ ቁ. (4)። |

| የግንኙነት መረጃ | |
|---|---|
| የማዕከሉ ስልክ ቁጥር፥ | 5602371 |
| የክፍሉ ስልክ ቁጥር፥ | 5603626 |
| ፌስቡክ: | www.facebook.com/AdalehCenter |
| ኢሜል፡- | info@adaleh-center.org |
| ድህረገፅ: | www.adaleh-center.org |

مركز عدالة لدراسات حقوق الإنسان
Adaleh center for human rights studies

PORTICUS

مركز عدالة لدراسات حقوق الإنسان
Adaleh center for human rights studies

PORTICUS

# ለቤት ሰራተኞች የወጡ መመሪያዎች (ዮርዳኖስ)



Designed by: A. A.GH